**አዋጅ ቁጥር ——/2011**

**<u>የዕርቀ–ሰላም ኮሚሽን ማቋቋምያ /ረቂቅ/ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዪ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅ ማውረድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጡትን መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ እና ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ጉልህ የመብት ጥሰቶችን ምንነት በግልጽ መለየት አስፈላጊ ስለሆነ እና ለእርቀ ሰላሙም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ፤

በተለያዩ ጊዜዎቸ እና የታሪክ አጋጣሚዎች የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ሌላ በደል ተጠቂዎች የሆኑ ወይም ተጠቂዎች ነን ብለው የሚያምኑ ዜጎች በደላቸውን የሚናገሩበትና በደል ያደረሱ ዜጎች ላደረሱት በደል በግልፅ በማዉጣት የሚፀፀቱበት እና ይቅርታ የሚጠይቁበት መንገድ በማበጀት እና እርቀ ሰላም በማዉረድ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ፤

ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እየፈረሰ የሚሰራ ሳይሆን እየተገነባ የሚሄድ ስርዓት ለመፍጠር፣ ዲሞክራሲያዊ ሀገርና ማህበረሰብ ለመገንባት ሰፊና ተቀባይነት ያለው የእውነትና፣የእርቅ እና የሰላም ዓላማ ያነገበ፣ለግጭትና ቁርሾ ምክንያት የሆኑትን ዝንፈቶች ምክንያቶችና የስፋት መጠን አጣርቶ እውነታውን በማዉጣት ተመልሰው እንዳይመጡ በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን የሚወስድና እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመነጭ ገለልተኛ እና ነጻ ኮሚሽን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታዉጇል

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “የዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር __________/2011” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>መቋቋም</u>**

1/ የዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2/ ኮሚሽኑ የራሱ ጽሕፈት ቤት ፣በጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

3/ የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ሕጋዊ ሰዉነት አለው፡፡

4/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

3. **<u>የኮሚሽኑ አባላትና አሰያየም</u>**

1/ የኮሚሽኑ አባላት ቁጥር በመንግስት የሚወሰን ይሆናል፡፡

2/ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ፣ምክትል ሰብሳቢ እና ሌሎች አባላት በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ይሰየማሉ::

3/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የኮሚሽኑ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል::

4. **<u>የኮሚሽኑ ዓላማ</u>**

የኮሚሽኑ ዓላማ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ሰላም፣ ፍትህ፣ ብሄራዊ አንድነትና መግባባት፣ እንዲሁም እርቅ እንዲሰፍን መስራት ነው፡፡

5. **<u>የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር</u>**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ስራዉን በሚመለከት ማንኛዉም ያገባኛል የሚል ሰው ወይም አካል ሃሳቡ እንዲያቀርብ ጥሪ ማቅረብ እና አስፈላጊውን ምዝገባ ማካሄድ፤

2/ ስራዉን በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ተደራሽ፣ አሳታፊ፣ ሁሉም አካል እኩል ተደማጭ የሚሆንበት የዕርቀ-ሰላም ውይይት መድረክ ማዘጋጀት፤

3/ የተለያየ ዐቋም የያዙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየትና ለሃገራዊ እርቅ መሰረት የሚሆኑ የጋራ መርህዎችንና እሴቶችን መለየት፤

ECLN

4/ የግጭቶችንና የሙብት ጥሰቶቹን መነሻ ምክንያት ለመለየት፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶችን፣ የተጎጂዎችንና ጥፋተኞቸን አስተያየት በመወሰድ ምርመራ ማካሄድ፤

5/ ለሰራው አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛዉንም የሰነድ ወይም ሌላ መረጃ ከመንግስትም ይሁን ከማናቸውም ሌላ አካላት የመቀበልና በፈለገው ጊዜ እንዲያቀርቡ የማዘዝ፤

6/ ሀላፊነቱን ለመወጣት የማናቸውንም ተቋም ይዞታ የመጎብኘት፣ በጉብኝቱም ጊዜ የሚያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃዎችና፣ ሰነዶችን ቅጂ የመውሰድ፤

7/ መረጃ ለመሰብሰብ በተናጠልም ሆነ በቡድን፣ በምስጢርም ሆነ ለህዝብ ክፍት በሆነ ሁኔታ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ መጥሪያ በመላክ ማንኛዉም ሰው እንዲቅርብ የማዘዝ እና ቃሉን በቃለ መሃላ እንዲሰጥ የማድረግ፤

8/ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንድሁኔታው የፌደራልም ሆነ የክልል ፖሊስ እገዛ የማግኘት፤

9/ በምርመራው የሚደርስባቸውን መደምደሚያዎች እንደሁኔታው በየጊዜው ለህዘብና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማሳወቅ፤እና

10/ በህዝቦች መካከል የተፈጠረ ልዩነት እንዲረግብ እና መግባባት እንዲፈጠር እርቀ ሰላም እንዲወርድ የማድረግ።

6. <u>**የኮሚሽኑ ስብሰባ**</u>

1/ የኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ በየአስራ አምስት ቀኑ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

2/ ከኮሚሽኑ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

3/ የኮሚሽኑ ምክረ ሃሳቦች በስምምነት ያልፋሉ፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚሽኑ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. <u>**የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**</u>

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ:-

1/ ኮሚሽኑን ይመራል

2/ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴዉን በበላይነት ይመራል

3/ ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የምድባል

4/ ኮሚሽኑን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል

8. <u>**የኮሚሽኑ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**</u>

የኮሚሽኑ ምክትል ሰብሳቢ:-

1/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢዉን ተክቶ ይሰራል፤

2/ በሰብሳቢው የሚሰጡት ተግባራት የፈጽማል::

9. <u>**የጽሕፈት ቤቱ አቋም**</u>

የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት:-

1/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ሃላፊና ፤እና

2/ አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፤

3/ የኮሚሽኑ ዋና ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሩቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል::

10. <u>**የጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር**</u>

ECLN

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1/ ለኮሚሽኑ አጠቃላይ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣል፤

2/ ለኮሚሽኑ የህዝብ ተሳትፎና ምክክር መድረኮችን የሎጅስቲክስ ድጋፍ ይሰጣል፤

3/ የኮሚሽኑን ቃለ ጉባኤዎችን፣ ውሳኔዎችንና ሌሎች ሰነዶችን በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል ፤

4/ የኮሚሽኑን ስራ ለማሳለጥ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል።

11. **<u>የጽህፈት ቤት ሃላፊ</u> <u>ስልጣንና ተግባርና</u>**

የጽ/ቤቱ ሃላፊ :-

1/ የጽሕፈት ቤቱ ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል፤

2/ የኮሚሽኑ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3/ ጽሕፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል::

12. **<u>የኮሚሽኑ ገለልተኝነት</u>**

ኮሚሽኑ ስራውን በነፃነትና በገለልተኝነት ያከናውናል።

13. **<u>የስራ ዘመን</u>**

1/ የኮሚሽኑ የስራ ዘመን እስከ 3 ዓመት ነው።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም የኮሚሽኑን የስራ ዘመን እንድሁኔታው ሊራዘም ይችላል።

14. **14. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚያቀርበው ማንኛውንም ህጋዊ ጥያቄ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

15. **15. <u>በጀት</u>**

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

16. **16. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል::

2/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ::

17. **17. <u>ጠቋሚዎችና ምስክሮችን ስለመጠበቅ</u>**

1/ ማንኛዉም ሰው በኮሚሽኑ ፊት ቀርቦ በሚሰጠው ቃል መሰረት ክስ ሊመሰረትበት እንደዚሁም የሰጠው ቃል በእርሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብበት አይችልም::

2/ ለጠቋሚዎችና ለምስክርች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ ሕግ ለኮሚሽኑ ቃላቸው እና መረጃ ለሚሰጡ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል::

18. **18. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ፤ ህዳር ….. ቀን 2011 ዓ.ም

ECLN

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊዲ ሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት

ECLN